# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**:- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## <u>ዜና ዘገባ</u>

**መጋቢት 3 ቀን 2003 ዓ.ም.**

**በጅማ በተከሰተው ብጥብጥ አንድ ሰው ተገደለ 55 ቤቶች ጋዩ፤**

**የሙስሊም አባቶች ድርጊቱን ወያኔ መፈጸሙን በይፋ አጋለጡ፤**

**የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ከስልጣናቸው ተባረሩ፤**

**ለባለስልጣናቱ በመቶ ሚሊዮን ብር ወጪ አዲስ ስልጠና ሊሰጣቸው መሆኑ ተጋለጠ፤**

በምዕራብ ኦሮሚያ ዞን በጅማ ከተማ አቅራቢያ በሚገኘው አሰንዳቦ በተባለች አነስተኛ ከተማ በተቀሰቀሰ የጥፋት ዘመቻ አንድ ሰው ሲገደል በሺህዎች የሚቆጠሩት ቤት ንብረታቸውን ጥለው መሰደዳቸው ታወቀ::

ወያኔ በሚደርስበት ውስጣዊና ውጫዊ ጫና ምክንያት የራሱን ልጣን ለማደላደልና የአገዛዝ እድሜውን ለማራዘም ሲል በብሔር እና በሀይማኖት እየከፋፈለ ለማጋጨት ባወጣው እቅድ መሰረት ተግባራዊ ያደረገው ይሄው የጥፋት ተልዕኮ ባለፈው ሳምንት በጅማ አቅራቢያ በሚገኙ መንደሮች በተፈጠረ ውዝግብ ከ55 በላይ ቤተክርስቲያኖች እና ቤቶች መጋየታቸውም ታውቆዋል::

እራሳቸውን አክራሪ የሙስሊም እምነት ተከታዮች ነን በሚሉ ቡድኖች የተጀመረው የጥፋት ተልዕኮ ለተከታታይ ሶስት ቀናት የተካሄደ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ በነዚሁ ቀናት ውስጥ አንድ የክርስትና እምነት ተከታይ በተኛበት ቤቱን ቆልፈው ጋዝ አርከፍክፈው ከነቤቱ ያቃጠሉት ሲሆን ሌሎች 20 መኖሪያ ቤቶችን ከነ ሙሉ እቃዎቻቸው እንዳወደሙ ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አረጋግጦዋል::

ወያኔ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም ሲል ብቻ ለዘመናት ታፋቅሮና ተከባብሮ በኖረው ህዝብ መሀል እልቂት እና ጥፋት እንዲፈፀም መርዘኛ ፕሮፓጋንዳ መንዛት ከጀመረ ዓመታት የተቆጠሩ ቢሆንም ከቅርብ ግዜ ወዲህ ግን በአዲስ መልክ በጀመረው የጥፋት ተልዕኮ ሰሞኑን በጅማ አካባቢ በስፋት እየሰራበት መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

በዚህም መሰረት በደህንነት ሹሞቹ በእነ ጌታቸው አሰፋ የበላይነት የሚመራ ቡድን በህዝቡ ውስጥ ተበትኖ እጅግ አደገኛ እና መርዘኛ ፕሮፓጋንዳ ከአንድ ወር በፊት በአዲስ አበባና በሌሎችም ከተሞች ሲነዛ የነበረ መሆኑን የጠቆመው ጉዳዩን በአንክሮ የሚከታተለው የደረሰን ዘገባ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ያሰቡት ተንኮል....... የወጠኑት ሴራ....... ውጤታማ አልሆን ሲላቸው በምስጢር አሰለጥነው እና አደረጅተው እራሱን የአክራሪ ሙስሊም ሀይማኖት ቡድን አስመስለው በጅማ አካባቢ አስርገው በማስገባት እጅግ ዘግናኝ እልቂት እና ውድመት እንዲደርስ ከማድረጋቸውም በተጨማሪ የመላው ሀገሪቱ ህዝብ ትኩረት ለመሳብ ያደረጉት መሆኑን ይሄው ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል::

ህዝቡ በፖለቲካ.... በማህበራዊ ......በኢኮኖሚ...... በተለይ በኑሮ ውድነት ከፍተኛ ችግር ውስጥ ከመውደቁ የተነሳ አመፅ ሊያነሳ ይችላል በሚል ፍራቻ የተነሳ ህዝብን ከህዝብ እያጋጩ መልሰው እነሱ ከሳሽ..... ዳኛ...... እና አሳሪ እና ፈቺ ለመሆን ባወጡት እቅድ መሰረት የአዲስ አበባው አልሳካ ሲላቸው በጅማ አቅራቢያ እየፈጸሙ መሆኑን ዘገባው አብራርቶዋል::

ሐሙስ የካቲት 24 ቀን 2003 ዓም ከጅማ ከተማ 50 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው አሰንዳቦ ከተማ ከቀኑ 8 ሰዓት ላይ ሲሆን ነዋሪዎችዋ እንደወትሮው ግዜ ሁሉ ደፋ ቀና እያሉ በሚገኝ ብት ሰዓት ከየት መጡ ሳይባል በጥምጥም ፊታቸውን በሸፈኑ 50 የሚሆኑ የታጠቁ ሰዎች ድንገት ደርሰው በከተማዋ የቃለ ህይወት.....የሙሉ ወንጌል....የመካነ እየሱስ እና የአድቬንቲስት ቤተክርስቲያኖችን ጋዝ እያርከፈከፉ ከማቃጠላቸውም በተጨማሪ የክረትስትና እምነት አማኝ ቤቶችን አብረው መጋየታቸው ከአይን እማኞች የደረሰን ጥቆማ አረጋግጦዋል::

ሐሙስ ዕለት የጀመረው ይሄው የጥፋት ተልዕኮ በከተማዋ ዙሪያ በሚገኙ የቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ዘልቀው በመግባት መኖሪያ ቤቶችን እና ቤተ ክርስቲያኖችን በክብሪት እየለኮሱ ከማቃጠላቸውም በላይ በግልገል ግቤ ጭሪ ቀበሌ ነዋሪ የነበረ አንድ ግለሰብ ላይ ቤት ዘግተው በማቃጠላቸው አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ህይወቱ እንዲያልፍ መደረጉን ዘገባው ገልፆዋል::

ማንነታቸው እንዳይታወቁ እና እንዳይታዩ ፊታቸውን ጠምጥመው የመጡት እነዚሁ የወያኔን ተልዕኮ ፈጻሚ ኃይሎች በተሰማሩበት የጥፋት ቦታዎች ሁሉ ያገኙትን ቤት እና ንብረት

እየለኮሱ ከማጋየታቸውም በላይ አዛውንቶችን እና አሮጊቶችን በዱላና በአለንጋ እንደ ህፃን እየገረፉ ሲያሰቃዩዋቸው እንደነበረም ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል።

ወያኔ በአሁኑ ሰዓት በተፈጠረበት በኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካው እንዲሁም በአሁኑ ወቅት በኑሮ ውድነት ጥያቄ በገባበት አጣብቂኝ ምክንያት እራሱ አሰልጥኖ ባሰማራቸው ወንበዴዎች አማካኝነት በሙስሊሙ እና በክርስትና ሐይማኖት ተከታዮች ዘንድ ብጥብጥ እንዲነሳ እና በዚህ ፋታ ለማግኘት አልፎ ተርፎ የህዝቡን የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር እየሰራ መሆኑን የጉዳቱ ሰለባዎች የተረዱ ከመሆኑም በላይ የሙስሊም እምነት አባቶች በበኩላቸው ይሄንን ተግባር የሚፈፅም ልዩ ተልዕኮ ያለው በመሆኑ ወያኔ እራሱ ምስጢሩን ይፋ ሊያደርገው ይገባል ሲሉም ማሰሳቢያ ጭምር መስጠታቸው የወያኔን ገመና ያጋለጠ መሆኑ ታውቆዋል።

ኦሮሞውን ከሱማሌው...አፋሩን ከአማራው...ከንባታውን ከወላይታው...አኙዋኩን ከኑዌሩ...ራያውን ከአክሱሙ .....እያላተሙና እያጋጩ የበሰበሰና የተደረተ ስልጣናቸውን ለመቀጠል እየጣሩ ባለት በአሁኑ ወቅት የጀመሩት አደገኛ ህዝብ ጨራሽ ሴራ በህዝቡ ትግል ሊከሽፍ ይገባል ያሉት የሙስሊሙ አባቶች ለዘመናት አብረን ተሳስረን የኖርን የአንድ ሀገር ዜጎች ዛሬ በከፋ ችግር ላይ ባለንበት ወቅት እና ችግሮች በተነባበረብን ግዜ ምን ተገኝቶ ነው ይህንን ተግባር በወገኖቻችን ላይ ልንፈጽም የሚያነሳሳን? ሲሉም ጥያቄ ሰንዝረው ወያኔ ከዚህ ቀደም በዚሁ በጅማ አሰልጥኖ ባሰማራቸው የጥፋት ኃይሎች አማካኝነት ብዙ ህዝብ በእሳት ነድዶ እንዲቃጠል ያደረገ በመሆኑ አሁንም እራሱ ያሰማራቸው ቡድኖች መሆናቸው ጥርጥር የለንም ሲሉ አጽንዖት ሰጥተው መግለፃቸውን የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል።

አክለውም በክርስቲያን ወገኖቻችን ላይ የተፈጸመው ዘግናኝ እና አሰቃቂ ግፍ እጅግ የሚያንገበግብ ከመሆኑም በላይ ያስቆጫል ያሉት እነኚሁ የእስልምና እምነት አባቶች መቼም ቢሆን መቼ አውነቱ መውጣቱ የማይቀር ነው ሲሉ በቁጭት መግለፃቸውን ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል።

በወያኔ ስልጠና በተሰጣቸው እና የጥፋት ተልዕኮ በተሰጣቸው የእስልምና እምነት አማኝ ናቸው በተባሉ ታጣቂዎች ሐሙስ የካቲት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ከቀኑ 8 ሰዓት ላይ የጀመረው ጥቃት እስከ ቅዳሜ የካቲት 26 ቀን 2003 ዓ.ም ለሶስት ከታታይ ቀናት ድረስ ቀጥሎ የነበረ ሲሆን በነዚህ ቀናት ውስጥ አንድ ሰው ሲገደል ከ6 ሺህ በላይ የአካባቢው ነዋሪዎች ቤት ንብረታችን ጥለው ገመሱ ወደ ከንባታና ሀዲያ ሲሻገሩ ሌሎቹ ወደ ጅማ ከተማ መግባታቸው ታውቆዋል።

ከዚህም ሌላ ከ35 ቤተክርስቲያኖች እና ከ20 መኖሪያ ቤቶች በላይ ከነሙ ንብረቶቻቸው የተቃጠሉ ሲሆን ችግሩ ሲከሰት በስፍራው የደረሰውን የኦሮሚያ ፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ኃይል በአስቸኩዋይ ከቦታው ነቅሎ እንዲወጣ መደረጉ የወያኔ ቡድን ሆን ብሎ ያስፈጸመው መሆኑን የሚያሳይ ነው ሲል ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል።

የኦሮሚያ ፈጥኖ ደራሽ ከጅማ ከተማ መጥቶ ደርሶ የነበረ ቢሆንም ልዩ እገዛ እና ሽፋን እንዲሰጥ ትዕዛዝ የተሰጠው የፌዴራል ፖሊስ ኃይል ግን ፈጥኖዎቹን ይተካ በሚል እነሱን አባርሮ የተረከበ ቢሆንም ቤት እና ቤተክርስቲያኖች ሲቃጠሉ እያየ እንዳላየ ከመሆኑም በላይ አንድም ከጥፋት

ኃይሎች መሀከል ለመያዝ ጥረት አለማድረጉ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቢሮ ያቀናበረው መሆኑን ሊያረጋግጥ እንደሚችል ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

ችግሩ ተስፋፍቶ እጅግ አሰቃቂ ሁኔታዎች ከተከሰቱ ብሎም በአለም አቀፍ ሚዲያ ከተነገረና ከታወጀ በሁዋላ ለማስመሰል የመከላከያ ሰራዊት ጭምር በስፍራው አስገብቶ አጥፊዎችን አድነን እንይዛለን እያለ የወያኔ ቡድን ቢደነፋም ወያኔ እራሱ የፈጸመው መሆኑን የአካባቢው ሰዎች አስረግጠው እየተናገሩ መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ዘገባም ገልፆዋል፡፡

በ1999 ዓ.ም በተመሳሳይ በዚሁ በጅማ አቅራቢያ በሚገኙ ትናንሽ ከተሞች በተፈጠረ ችግር እጅግ ቁጥራቸው የበዛ ዜጎች በቆንጨራና በጀራ አንገታቸው ታርደው የተገደሉ ከመሆኑም በላይ መኖሪያ ቤት እና ቤተክርስቲያኖች ተቃጥለው ብዙ ንብረት መውደሙ የሚዘነጋ አይደለም፡፡

በሌላ ዜና ወያኔ የስልጣን እድሜዬን ያራዝሙልኛል በሚል ከየዩኒቨርስቲ በግዳጅ መልምሎ ወደ ስራ ያሰማራቸው አዳዲስ ሰራተኞች እና ነባር በረሀ አመጣሽ ካድሬዎች መሀከል በተከሰተ ያለመግባባት የተነሳ የወያኔ ቡድን እንደ ብራና ተወጥሮ እንደሚገኝና ግምገማውንም ውስጥ ውስጡን እያደረገ መሆኑ ተገለፀ፡፡

የወያኔ ተለጣፊ ድርጅቶች በሆኑት በኦህዴድ.... በብአዴን...... በዴኢህዴን ባለስልጣናት እና ካድሬዎች መሀከልም ጥብቅ የሆነ ምስጢራዊ ግምገማ እየተደረገ ሲሆን በተለይ ከኦህዴድ እና ከደኢህዴን አዳዲስ እና ነባር ካድሬዎች ከስልጣናቸው እየተባረሩ መሆኑ ታውቆዋል፡፡

የአምስት ዓመቱን የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ እውቀትና ችሎታ ያስፈልጋል በጭፍን ሀገር እና ህዝብን ማሳመን እና መምራት አይቻልም ስትሉ ነበር የተባሉ አዳዲስ ካድሬዎች በተደረገባቸው ግምገማ ከስራ የተባረሩ ከመሆኑም በተጨማሪ ጥፋት ተፈልጎባቸው እንዲከሰሱ መወሰኑን ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ኦህዴድ በአዳማ ላይ ለሰባት ቀናት ባደረገው ጥብቅ ምንጠራ 9 ከፍተኛ ባለስልጣናትን ያባረረ ሲሆን ከእነሱ መሀከልም ህዝብን ሊያሳምፁ ነበር የተባሉት የሙስና ክስ ተመስርቶባቸው በቅርቡ ወደ ዘብጥያ ሊያወርዱዋቸው መሆኑን ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በወያኔው ፖሊት ቢሮ አባሉ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ በኦሮሚያ ክልል ሬዝዳንት እና በኦህዴዱ ሊቀመንበር አለማየሁ አቶምሳ እና በምክትል ሊቀመንበሩ የመለስ አማካሪው ሙክታር ከድር ሰብሳቢነት የተደረገው ይሄው የባለስልጣናት መንጠራ 9 ዋና ዋና የተባሉ የክልሉ የቢሮ ኃላፊዎችን ያባረሩ ሲሆን ከነዚህ መሀከልም በቅርቡ እንዲከሰሱ ፋይላቸው መለስ ዜናዊ ጋ ቀርቦ እንደሚወሰንባቸው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡

በመስከረም ወር በተደረገው ሹም ሽረት አዲስ ወጣት ካድሬዎችን ወደ ስልጣን ማመጣት ተብሎ ኃላፊነት የተሰጣቸው እነዚሁ ተባራሪ የወያኔ ባለስልጣናት ነባር ከተባሉት ካድሬዎች ጋር በፍጹም መግባባት ካለመቻላቸውም በላይ የሚያነሱዋቸው ጥያቄዎች ለነመለስ የራስ ምታት

ሆኖባቸው የነበረ መሆኑን የጠቆመው የደረሰን ዘገባ ይህንን መሰረት አድርጎ በተደረገ ምንጠራ ከስልጣናቸው ሊባረሩ እንደቻሉ ገልጾ አንዳንዶቹም ነባር ባለስልጣን እንደሆኑም ታውቆዋል፡፡

ከተሾሙ ስድስት ወራትን ያላስቆጠሩት እነዚሁ ተባራሪ የኦሮሚያ ክልል ባለስልጣናት የፍትህ ቢሮ ኃላፊ ዮሐንስ ምትኩ...የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ ቶሎሳ ደደፉ....ምክትሉ ተስፋዬ አበበ.....የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወንድሙ ቢራቱ.....የመንገድና ትራንስርት ቢሮ ኃላፊ ሁሴን ገልገሉ.....የውሀ ቢሮ ኃላፊ ጀማል አባሶ.....ምክትሉ ግርማ ሰንበታ......የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ አሊዬ ዑመር ......የአዲስ አበባ ዙሪያ ዋና አስተዳዳሪ የነበረውና በአሁኑ ሰዓት የምዕራብ ሸዋ ዞን ዋና አስተዳዳሪ የነበረው ገላና ኑሬሳ መሆናቸውን የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡

ከስልጣናቸው በተነሱት ኃላፊዎች ምትክ ወዲያው ሹመት የተሰጠ ሲሆን ለአዲሶቹም ተሹዋሚዎች ከእነዚህ ግለሰቦች መማር አለባችሁ ሲሉም የወያኔ ፖሊት ቢሮ አባሎቹ እነ ኩማ ደመቅሳ መመሪያና ማስፈራሪያ እንደሰጠዋቸው ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በደኢህዴንንና በብአዴን ውስጥም ጥብቅ ግምገማ እየተደረገ ሲሆን ደኢህዴን በውጭ ጉዳይና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኃይለማርያም ደሳለኝ እና በክልሉ ፕሬዝዳንት በሽፈራው ሽጉጤ ሰብሳቢነት በአዋሳ ከተማ እየተካሄደ ሲሆን በቅርቡም ግምገማው እንዳበቃ ተንሳፋፊ እና ተሹዋሚ ባለስልጣናት እንደሚታወቁ ተጠቁሞዋል፡፡

ብአዴን በበኩሉ በባህርዳር ላይ ግምገማውን በአያሌው ጎበዜና በምክትሉ በኩል እያደረገ ሲሆን ማን እንደሚነሳና ማን እንደሚተካ የሚታወቀው በግምገማ ማጠናቀቂያው ላይ ነው ቢባልም በብአዴን ውስጥ እርስ በርስ መሞከሻሸት እንጂ መጠራረብ የሌለ በመሆኑ ብዙ አይጠበቅም ሲል የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡የወያኔ ተለጣፊ ድርጅቶች አውራ የሆነው ህወሀት ግን እስከ አሁን ድረስ ግምገማ ያልጀመረ መሆኑም ታውቆዋል፡፡

መለስ ዜናዊ በአንድ ጀንበር ጽፎ የበተነውን የአምስት ዓመት እድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ተግባራዊ እናደርጋለን እያሉ የብብታቸው ጸጉር እስኪታይ ድረስ እጃቸውን ሲሰቅሉ የነበሩትና ትርጉሙ ያልገባቸው የወያኔ ባለስልጣናት የእቅዱን ምንነት አልተረዱም በሚል በቅርቡ በመለስ ትእዛዝ እንደገና ወደ ስልጠና ሊገቡ እንደሆነ ተጠቆመ፡፡

ወያኔ ከበረሀ እስከ ዛሬ የተጉዋዘባቸው መንገዶች በሚል አዲስ መጽሀፍ መለስ ዜናዊ ያዘጋጀ ሲሆን በዚህ እና ቀድሞ በወጣው የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ ላይ ስልጠና እንዲሰጣቸው በታዘዘው መሰረት ከመጋቢት 5 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ለሁለት ወራት ለከፍተኛ የወያኔ ባለስልጣናት በሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ እንዲሰጣቸው እንደሚደረግና ዝግጅቱም እንደተጠናቀቀ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

ያወጣነውን አዲሱን እቅድ የገዛ ካድሬዎቻችን ሊተገብሩ ቀርቶ በአግባቡ ሊረዱ አልቻሉም...... ህዝቡም አልተቀበለውም..... ስለዚህ ከበረሀ ስንነሳ ጀምሮ ያሳለፍነውን ታሪክ የሚዳስስ አዲስ መፅሀፍ ማውጣትና ካድሬዎቹን ወጥሮ መያዝ የሚል እነ መለስ ዜናዊ ባወጡት ዕቅድ መሰረት በቅርቡ ከፍተኛ ባለስልጣናትን ወደ ስልጠና ሊያስገቡዋቸው መሆኑንም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በዚህ ስልጠና ላይ ከህወሀት... ከብአዴን.... ከኦህዴድ እና ከደኢህዴን በኮታ ተመርጠው ስልጠናውን እንዲከታተሉ ተደርጎ እነሱም በተዋረድ ለበታቾቻቸው ስልጠናውን እንደሚሰጡ ምንጮቹ ጠቁመው ለዚህም ይረዳ ዘንድ በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠር ብር በጀት መመደቡን ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡